30ኛ ዓመት ቁጥር 35
30th Year, No. 35

ባሕርዳር መጋቢት 16 ቀን 2018 ዓ.ም
Bahir Dar, March 25, 2026

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG
of the Amhara National Region Council in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the Auspices of the Council of the Amhara National Region

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 732.78 ብር
Unit Price Birr 732.78 ብር

ማዉጫ

አዋጅ ቁጥር፫፻፲፩/፪ሺ፲፰ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሻ ኮሚሽን ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ

Content

Proclamation No. 311/2026 In the Amhara National Regional State the Revised Militia Commission Establishment, Powers and Duties Determination Proclamation

አዋጅ ቁጥር፫፻፲፩/፪ሺ፲፰ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሻ ኮሚሽን ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ

ለፌደራሉም ሆነ ለክልሉ ሕገ-መንግሥትና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ታማኝ፣ ታዛዥና ተገዥ የሆነ፣ የተጣለበትን ሕገ-መንግሥታዊ ተልዕኮበብቃት መወጣት የሚችልና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ባደረገ መልኩ ተልዕኮዉን የሚፈጽምና የሚመራ የሚሊሻ እና የሰላም አስከባሪ ሃይል ማደራጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

Proclamation No. 311/2026
A Proclamation Issued to Determin the Revised Militia Commission Establishment, Powers and Duties of the Amhara National Regional State

Whereas, it is appropriate to organize a militia and peacekeeping force that is loyal, obedient and submissive to both the federal and regional constitutions and constitutional systems, capable of effectively fulfilling its constitutional mandate, and that carries out and leads its mission in a manner based on the actual conditions of the region;

ከዚህ በፊት በተበታተነ ሁኔታ በሥራ ላይ ያሉትን የሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፲፱፺፰ እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፺፭ን በአንድ የሕግ ማዕቀፍ በማጠቃለል በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ እና የተቋሙን አደረጃጀት ከሚሰጠዉ ሰፊ አገልግሎት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ በማስፈለጉ፤

እነዚህ አዋጆች ሥራ ላይ ከዋሉ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠሩ በመሆናቸው የተፈጠሩ አዳዲስ ክልላዊ ዕድገቶችን፣ አዳጊ ፍላጎቶችን፣ የአገራችንና የክልላችንን እንዲሁም ቀጠናዊ ሁኔታዎችንና የወደፊት አዝማሚያዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ የሕግ ማዕቀፍ መኖርን የሚጠይቅ በመሆኑ፤

የኮሚሽኑ አመራሮችና ባለሙያዎች የጡረታ ዕድሜን፣ የሰላም አስከባሪና ሚሊሻ አባላት ደግሞ የአገልግሎት ዘመን፣ ጥቅማጥቅሞች፣ ማበረታቻዎችና ሽልማቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች በሕግ ማዕቀፍ ምላሽ ሊያገኙ እንደሚገባ በመታመኑ፤

የአማራ ብሄራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ ፫ (፩) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ረቂቅ አዋጅ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የተሻሻለው የሚሊሺያ ኮሚሽን ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፪ሺ፲፮ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡ ፡

Whereas, it is necessary to consolidate the previously fragmented Militia Office Establishment Proclamation No. 13/1998 and Amendment Proclamation No. 1991/1995 into a single legal framework, making them easily accessible, and to align the organization of the institution with the wide range of services it provides;

Since these proclamations have been in effect for many years, it is necessary to have a legal framework that takes into account new regional developments, emerging needs, our country and region, as well as sub- continent of regional conditions and future trends;

Whereas, it is believed that issues related to retirement age and of the leaders and proffessionals of the commission and service period, benefits, incentives, and awards for peacekeepers and militia members should be addressed within the framework of the law of the leaders and experts of the Commission.

Now therefore, the Amhara Region Council hereby issued this proclamation vested in power under Article 49, Sub-Article 3 (1) of the revised regional Constitution.

PART ONE

General Provisions

1. Short Title

The revised millissia commission establishment, powers and duties proclamation N. o 311 2026 This Proclamation may be cited as **"Proclamation No. 311/2026 Determining the Establishment, Powers and Duties of the Amended Militia Commission"**.

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/"ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ነው፤

፪/ "ኮሚሽን ወይም "ኮሚሽነር ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሚሊሻ ኮሚሽን ወይም የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ነው፤፤

፫/"ዋና መምሪያ እና ዋና መምሪያ ኃላፊ" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በኮሚሽኑ ስር በሚገኙ የስራ ክፍሎችወታደራዊ ጠባይ ያላቸው ከፍተኛ የሥራ መደቦች እና በዚሁ የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ በኃላፊነት የሚሠራ ሰው ነው፤

፬/ "መምሪያ" እና "መምሪያ ኃላፊ" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በኮሚሽኑ ሥር በሚገኙ ዞኖች እና በዞን ደረጃ በተዋቀሩ ከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረ መምሪያ እና የዚሁ መምሪያ ኃላፊ ነው፤

፭/ "ጽሕፈት ቤት"ማለት የወረዳ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ወይም የከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተማ ሚሊሻ ጽህፈት ቤት ማለት ነው፤

፮/ "ዋና ክፍል" እና "ዋና ክፍል ኃላፊ" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በኮሚሽኑ ውስጥ ወታደራዊ ጠባይ ያላቸው ከዋና መምሪያ ቀጥሎ እና ከዞን መምሪያ ቀጥሎ ያሉ ከፍተኛ የሥራ መደቦች እና በዚሁ የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ በኃላፊነት የሚሠራ ሰው ነው፤

፯/ "ክፍል" እና "ክፍል ኃላፊ" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በኮሚሽኑ ሥር በሚገኙ ዞኖች ወይም በዞን ደረጃ በተዋቀሩ ከተማ አስተዳደሮች ስር ለተደራጁ ወረዳ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤቶች እና ክፍለ ከተማ ሚሊሻ ጽ/ቤቶችወታደራዊ ጠባይ ያላቸዉ ከፍተኛ የሥራ መደቦች እና በዚሁ የስራ መደብ ላይ ተመድቦ በኃላፊነት የሚሠራ ሰው ነው፤

2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ **"Bureau"** means the Peace and Security Bureau of the Amhara National Regional State;

2/ **"Commission" or "Commissioner"** means the Militia Commission of the Amhara National Regional State or the Commissioner of the Commission, respectively;

3/ **"Main Department and Head of Main Department"** means, respectively, the senior positions of a military nature in the departments under the Commission and the person assigned to such positions and responsible for such positions;

4/ **"Department" and "Head of Department"** means, respectively, a department and the head of such department organized in the zones under the Commission and in the city administrations organized at the zonal level;

5/ **"Office"** means the office of the Woreda Militia or the office of the Sub-City Militia of the City Administration;

6/ **"Main Section" and "Head of Main Section"** mean the highest positions of military nature in the Commission after the Main Department and after the Zone Department, respectively, and the person assigned to and responsible for such positions;

7/ **"Section" and "Section Head"** mean the highest positions of military nature in the Woreda Militia Offices and Sub-City Militia Offices organized under the Zones or under the City Administrations organized at the Zone level, respectively, and the person assigned to and responsible for such positions;

፰/ **"የኮሚሽን አመራር"** ማለት በተዋረድ የተደራጀ እና ወታደራዊ ጠባይ ባላቸው ወይም በሲቪልየሥራ መደቦች በየትኛዉም የአደረጃጀት ዕርከን ተመድቦ ወይም በኃላፊነት የሚሠራ ሰው ነው፤

፱/ **"ባለሙያ"** ማለት መሠረታዊ የሚሊሻ ሥልጠና አጠናቆ ቃለ-መሃላና የቅጥር ውል ፈጽሞ እንደማንኛውም መለዮ ለባሽ ሙሉ መብቱ ተጠብቆ በየትኛውም ደረጃ በኮሚሽኑ ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ደመወዝተኛ ሠራተኛ ነው፤

፲/ **"መለዮ ለባሽ"** ማለት የሚያስፈልገውን የሚሊሻ ስልጠና የወሰደ እና ሚሊተሪ ሆኖ የተመደበ ማንኛውንም ጥቅማ ጥቅም የሚያገኝ ደመወዝተኛ ሰው ነው፤

፲፩/ **"የሚሊሻ ቀጠና አስተባባሪ"** ማለት በቀጠና ደረጃ ተመድቦ የሰላም አስከባሪና የቀበሌ ሚሊሻን በኃላፊነት የሚመራ ደመወዝተኛ ሠራተኛ ነው፤

፲፪/ **"ሰላም አስከባሪ"** ማለት ከልማት ተግባሩ ሳይለይ ከሚሊሻው መካከል የተሻለ ብቃት ያላቸውን በመመልመልና ተጨማሪ የሰላም አስከባሪነት ሥልጠና ወስዶ፣ በወታደራዊ አደረጃጀት ውስጥ ታቅፎ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ለጸጥታ ስራ በሚሰማራበት ወቅት ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም እየተከፈለው ሕግ ለማስከበር ቅድሚያ ስምሪት የሚወስድና አገልግሎት ለመስጠት የፈቀደ ሰው ነው፤

፲፫/ **"የሚሊሻ አባል"**ማለት ከመደበኛ ሥራው ወይም ከልማት ተግባሩ ሳይነጠል በመንግሥት ወይም በግሉ በታጠቀው የጦር መሣሪያ ወይም ያለ ጦር መሣሪያ የአካባቢውን ሰላምና ጸጥታ ለማስከበር በማሕበረሰቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ተመልምሎ፣ መሠረታዊ የሚሊሻነት ሥልጠና ወስዶ፣ በሚሊሻ አደረጃጀት ውስጥ ታቅፎ፣ ምንም ዓይነት ደመወዝ ሳይከፈለው የሚሊሻነት አገልግሎት ለመስጠት የፈቀደ ሰው ነው፤

8/ **"Leaders of the Commission"** means a person assigned or responsible for any level of organization in a hierarchically organized and military nature or civilian position;

9/ **"Professional"** means a salaried employee who has completed basic militia training and has taken the oath and employment contract, and who is serving in the commission at any level, with full rights and privileges as any other civilian;

10/ **"Soldier"** means a salaried employee who has received the required militia training and is entitled to any benefits of being assigned as a military officer;

11/ **"Militia Sub-Wereda Coordinator"** means a salaried employee who is assigned to the sub-Wereda level and is responsible for peacekeeping and managing the kebele militia;

12/ **"Peacekeeper"** means a person who, regardless of his development duties, has recruited the best qualified people from among the militia and has undergone additional peacekeeping training, has been integrated into the military organization, has been assigned to provide priority employment for law enforcement, is paid a salary and benefits as necessary, and has agreed to provide service;

13/ **"Militia member"** means a person who, regardless of his regular work or development duties, has been recruited by direct participation of the community to maintain peace and security in the area, with weapon of his own or given by the government or without weapons, has undergone basic militia training, has been integrated into the militia organization, and has agreed to provide militia service without being paid any salary;

፲፬/ **"አደረጃጀት"** ማለት የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባላት በክፍለ ጦር ፣ በሻለቃ፣ በሻንበል፣ በመቶ እና በጓድ ተደራጅቶ በዕዝ የሚመራ የወታደራዊ አደረጃጀት ነው፤

፲፭/ **"ግዳጅ"** ማለት ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ፣ ባለሙያ ፣ የሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል መሠረታዊ የሚሊሻነት ሥልጠና ወስዶ ቃለ-መሃላ ከፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ በማንኛውም ምክንያት እስከሚሰናበትበት ጊዜ ድረስ በተናጠል ወይም ከፌዴራልና ከክልል የጸጥታ ኃይሎች ጋር በጥምረት የሚያከናውነው ማንኛውም ዓይነት አካባቢያዊ፣ ክልላዊና ሃገራዊ ይዘት ያለው የስምሪት ተግባር ነው፤

፲፮/ **"በክብር የተሰናበተ"** ማለት የትኛውም ዓይነት የዲስፕሊን ጉድለት ሳይኖርበት ተልዕኮውን በአግባቡ ተወጥቶ በዚህ አዋጅ ወይም አግባብነት ባለው ደንብና መመሪያ መሠረት የተሰናበተ ሰው ነው፤

፲፯/**"የጸጥታ ተቋም"** ማለት የሃገር መከላከያ ሰራዊት፣ የፌዴራል ፖሊስ፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የክልሉ ሰላምና ፀጥታ ፣ የክልል ፖሊስ፣ የማረሚያ ቤት ፖሊስ እና የክልሉን የሚሊሻ ኮሚሽን የሚመለከት ነው፤

፲፰/ **"የጦር መሣሪያ አስተዳደር"** ማለት በክልሉ ውስጥ የጦር መሣሪያ ለሚያስፈልጋቸው የሰላም አስከባሪ፣ የሚሊሻ አባላት፣ የኮሚሽኑ አመራሮች፣የሰላም እና ፀጥታ አመራሮች ትጥቅ የማቅረብ፣ የማስታጠቅ፣ የትጥቅ ፈቃድ መታወቂያ የመስጠት፣ የማደስ፣ የመሰረዝ፣ የመዉረስ፣ አጠቃቀሙን የመከታተልና የመቆጣጠር ሂደት ነው፤

14/ "Organization" means a military organization in which peacekeepers and militia members are organized into battalions, squadrons, companies, and units and are led by command;

15/ "Mission" means any deployment activity of any kind, local, regional, or national nature, undertaken by any member of the Commission, professional, peacekeeper, or militia member, from the time he or she takes the basic militia training and takes the oath of office until the time he or she is discharged for any reason, either individually or in conjunction with federal and regional security forces;

16/ "Honorably discharged" means a person who has properly discharged his duties without any disciplinary misconduct and has been discharged in accordance with this Proclamation or relevant regulation and directive;

17/ "Security Institution" indicates the National Defense Force, Federal Police, National Intelligence and Security Service, Regional Peace and Security, Regional Police, Prison Police and the Regional Militia Commission;

18/ "Weapons Administration" means the process of providing weapons, equipping, issuing, renewing, cancelling of weapons license confiscating, monitoring and controlling the use of weapons to peacekeepers, militia members, commission leaders and peace and security leaders who need weapons in the region;

፲፱/ **"ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ"** ማለት በፌደራል የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ መሠረት የጦር መሣሪያን በክልል ደረጃ እንዲያስተዳድር ስልጣን በተሰጠዉ አካል የፈቃድ ደብተር በሌለዉ ወይም በየዘመኑ የታደሰ የፈቃድ ደብተር ባልተሰጠዉ ግለሰብ ወይም ተቋም በትጥቅነት የተያዘ ማንኛውም ዓይነት የጦር መሣሪያ ነው፤

፳/ **"ሲቪል ሠራተኛ"** ማለት በኮሚሽኑ ውስጥ በሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት በሚተዳደሩ የሥራ መደቦች የተቀጠረ ሰው ነው፤

፳፩/ **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፪/ በዚህ አዋጅ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ያካትታል፡፡

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፬. የአሠራር መርሆዎች

ኮሚሽኑ ሥራዎችን ሲሰራ የሚከተሉትን መርሆዎች መሠረት በማድረግ ይሆናል፦

፩/ ሰብዓዊ ክብር የተላበሰ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በዘር፣ በብሔር፣ በቀለም፣ በጸታ፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ ፣ በሐይማኖት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሐብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ባለማድረግ፤

፪/ የቡድንአሠራር መርህን በመከተል የጋራናየግል ተጠያቂነትንና ኃላፊነትን መውሰድ፤

፫/ በታማኝነትና በቅንነት መርህ በመመስረት የተሰጠን ኃላፊነት መወጣት፤

፬/ የአሳታፊነት፣ የተጠያቂነትና የግልጽነት መርህን መከተል።

19/ "Illegal weapons" means any type of weapon that is held as a weapon by an individual or institution that does not have a license or has not been issued a license renewed from time to time by the body authorized to manage weapons at the regional level in accordance with the Federal Weapons Administration and Control Proclamation;

20/ "Civil servant" means a person employed in the Commission in positions governed by the Civil Service Law;

21/ "Person" means any natural person or any body granted personal rights by law;

22/ Any reference to the male gender in this proclamation shall include a female.

3. Scope of Application

This proclamation shall apply to any member of the Commission's leadership, professionals, peacekeepers and militia members.

4. Principles of Operation

The Commission shall operate in accordance with the following principles:

1/ To treat people with dignity and respect without discrimination on the basis of race, ethnicity, color, sex, language, politics, religion, social origin, wealth, birth or other status;

2/ To take collective and individual responsibility and accountability based on the principle of teamwork;

3/ To fulfill the responsibilities assigned based on the principle of honesty and integrity;

4/ To follow the principle of participation, accountability and transparency.

ክፍል ሁለት

ስለ ኮሚሽኑ መቋቋም፣ ሥልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት

፭. መቋቋምና ተጠሪነት

፩/ የአማራ ክልል ሚሊሺያ ኮሚሽን "ከዚህ በኋላ " ኮሚሽን " እየተባለየሚጠራ አካል በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፤

፪/ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል፤

፮. ዋና መሥሪያቤት

፩/ የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያቤት ባህርዳር ከተማ ይሆናል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ቢኖርም ኮሚሽኑ እስከ ቀበሌ ባለው የአስተዳደር ዕርከን ድረስ የተዘረጋ የአደረጃጀት መዋቅር ይኖረዋል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የኮሚሽኑ አደረጃጀት የአካባቢውን አቀማመጥ አመችነትና የጸጥታ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ወታደራዊ የጦር ክፍል አደረጃጀት መርህን በመከተል በንዑስ ቀበሌ፣ በቀበሌ፣ በቀጠና ወይም በክላስተር፣ በወረዳ፣ በዞን የተዋቀረ አደረጃጀት ሊኖረው ይችላል።

፯. ዓላማ

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የሕዝቡን የነቃ ተሳትፎ በማረጋገጥ የክልሉን ሕገ-መንግሥትና ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓት ከማንኛውም ዓይነት ስጋትና ጥቃት መከላከል፤

፪/ የክልሉን ህዝብ ሰላምና ደህንነት ፣ የሕዝብ እና የመንግሥት የልማት ተቋማትን ከማናቸውም ዓይነት ጥቃት መከላከል፤

PART TWO

Establishment, Powers, Duties and Organization of the Commission

5. Establishment and Accountability

1/ The Amhara Regional State Militia Commission, hereinafter referred to as the "Commission", is hereby re-established;

2/ The Commission shall be accountable to the Bureau;

6. Head Office

1/ The Head Office of the Commission shall be at Bahir Dar City;

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1 of this Article, the Commission shall have an organizational structure extending to the administrative level of the kebele;

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles 1 and 2 of this Article, the organization of the Commission may be organized in sub-kebele, kebele, woreda or cluster, woreda, zone, taking into account the convenience of the local situation and the security situation, following the principle of military unit organization.

7. Objective

The Commission shall have the following objectives in accordance with this Proclamation:

1/ To protect the Constitution and the constitutional order of the region from any kind of threat and attack by ensuring the active participation of the people;

2/ To protect the peace and security of the people of the region, and the public and government development institutions from any kind of attack;

፫/ ለሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ፍጹም ታማኝና ታዛዥ የሆነ፣ በጠንካራ የሥራ ባህልና ሥነ-ምግባር የታነጸ፣ በሁሉም መስክ በሚኖርበት ማሕበረሰብ በአርአያነት የሚታይ የኮሚሽንአመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል መገንባት።

፰. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባራት

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ከክልል ጀምሮ በተዋረድ የሚገኙ የኮሚሽኑን አስተዳደር መዋቅርን ይዘረጋል፣ ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፣

፪/ የህዝቡን የነቃ ተሳትፎ በማረጋገጥ የክልሉን ሕገ መንግሥት እና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ከማንኛውም ዓይነት የፀረ ሰላም ኃይሎች ስጋትና ጥቃት ይከላከላል፣

፫/ ሕግ ያስከብራል፣ የመንግሥት ሕግና ፖሊሲዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

፬/ በየትኛውም የክልሉ አካባቢ የሚፈጠሩ ሕገወጥ ድርጊቶችን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ከሚመለከታቸው የጸጥታ አካላት ጋር በመሆን ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣

፭/ የተቋሙን አጠቃላይ የመፈጸም አቅም የመገንባትና ተጠብቆ እንዲቀጥል የማድረግ፣ አዳዲስ አቅሞችን የሚፈጥሩ ሥራዎችን ይሠራል፣

፮/ አጠቃላይ የኮሚሽኑን የሰው ኀይል ምልመላ፣ ሥልጠና፣ ግንባታ፣ አደረጃጀት፣ ትጥቅና ስምሪት ይወስናል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣

፯/ የኮሚሽኑን አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ የሰላም አስከባሪውንና የሚሊሻውን ሃይል ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነ-ልቦናዊ የግንባታ ሥራዎችን በልዩ ትኩረት ይመራል፣

3/ To build a Commission leadership, professionals, peacekeepers and militia members who are completely loyal and obedient to the constitutional system, who are built on a strong work culture and ethics, and who are seen as role models in all areas of society.

8. Powers and Duties of the Commission

The Commission shall have the following powers and duties:

1/ Establishes, organizes, coordinates, and directs the administrative structure of the Commission, starting from the region;

2/ Protects the Constitution and constitutional order of the region from any threat or attack by anti-peace forces by ensuring the active participation of the people;

3/ Enforces the law; implements and enforces government laws and policies;

4/ Monitors and controls illegal activities occurring in any area of the region, and ensures that legal action is taken in cooperation with the relevant security bodies;

5/ Carries out tasks that will build and maintains the overall operational capacity of the institution, and creates new capabilities;

6/ Determines; implements; and supervises the recruitment, training, capacity building organization, equipment, and deployment of the overall human resources of the Commission;

7/ Directs the military, political, and psychological building of the Commission's leaders, experts, peacekeepers, and militia forces with special attention;

፰/ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የሚገኙ የሚሊሻ ማሰልጠኛ ማዕከላት እንዲጠናከሩ ይሰራል፡

8/ In collaboration with relevant bodies, efforts will be made to strengthen militia training centers in the region.

፱/ የኮሚሽኑን መዋቅርና አጠቃላይ የሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ ሃይሉን ተልዕኮ የመወጣት ዝግጁነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የኢንስፔክሽን፣ የአመራር፣ የዕዝና ቁጥጥር ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ይገነባል፤ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፤

9/ Establishes, develops, and monitors the implementation of an inspection, management, and control system to ensure the readiness of the Commission's structure and the overall peacekeeping and militia force to carry out its mission;

፲/ ሚሊሻው እና ሰላም አስከባሪ ኃይሉ ለረጅም ጊዜ ከመደበኛ ተግባሩ ሳይነጠል በአካባቢው በሚካሄዱ ጸጥታ የማስከበር ስምሪቶችና በሌሎች መንግሥታዊ ሥራዎች ከሌሎች የጸጥታ አካላትና ሕዝብ ጋር ተቀናጅቶ የሚሠራበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

10/ Follows, controls and creates a favorable environment for the long-term operation of the militia and the peacekeeping force in the area, without being separated from their regular duties, in coordination with other security agencies and the public;

፲፩/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሃገር ሰላምና ደህንነት መረጋገጥ ከሃገር መከላከያ ሰራዊት ጎን ይሰለፋል፤

11/ When necessary, they shall stand alongside the National Defense Force to ensure the peace and security of the country;

፲፪/ የተቋሙን ጠቅላላ ንብት፣ በጀት እና የሰው ኀይል ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤ ይመራል፤ ጥቅም ላይ ያውላል፤

12/ Manages, controls, directs, and utilizes the total resources, budget, and manpower of the institution;

፲፫/ በተሰጠው ህግ የማስከበር ስልጣን መሠረት ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውርን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ለሕግ እንዲቀርቡ ያደርጋል፤

13/ Monitors, controls, and brings to justice the illegal transfer of weapons in accordance with the law enforcement authority granted to it;

፲፬/ የኮሚሽኑ አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ ሰላም አስከባሪዎች፣ የሚሊሻ አባላት እና ሌሎች ሲቪል ሠራተኞች አግባብ ባለው ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈቀዱና የሚፈቀዱ ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን ጥናቶችን በማድረግ ሰንዶ ለቢሮው በማቅረብ በመንግስት ሲፈቀድ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

14/ Conducts studies on the various benefits that are permitted and permitted by the relevant rules and regulations of the Commission, peacekeepers, militia members, and other civilian employees, and submits it to the office, and implements it when permitted by the government;

፲፭/ በመለዮ ለባሽ ምልመላና ቅጥር፣ በትምህርትና ሥልጠና፣ በዕድገት አሰጣጥ፣ በስንብት፣ በደንብ ልብስ አለባበስና ሌሎችተዛማጅጉዳዮች ላይ ክልል አቀፍ ረቂቅ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለቢሮው በማቅረብ በመስተዳድር ምክር ቤት ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

15/ Prepares and submits draft regional directives on recruitment and employment, education and training, promotion, dismissal, military dress and other related matters to the office and implements them upon approval by the Administrative Council;

፲፮/ ሚሊሻው እና ሰላም አስከባሪው በግዳጅ በተሰማራበት ወቅት ለሚደርስበት ጉዳት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ድጎማና ማበረታቻ እንዲያገኝ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን መረጃዎችን አደራጅቶ በመላክ እንዲከፈለው ያደርጋል፤

16/ Organizes and sends information to the relevant body so that the militia and peacekeepers can receive subsidies and incentives for the damage they suffer during their mission deployment in accordance with the relevant law;

፲፯/ ለሥራው የሚያስፈልጉ የአስተዳደር ሠራተኞችን በክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤

17/ Hires, manages and dismisses administrative staff required for their work in accordance with the regional civil service law;

፲፰/ የተቋሙን ሰብዓዊና ቁሳዊ ኀብት ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዘመናዊ የኀብት አስተዳደር ሥርዓቶችን በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

18/ Establishes and implements modern resource management systems that enable the management and controls of the institution's human and material resources;

፲፱/ የተቋሙን የመፈጸም ብቃት የሚያጎለብቱና መልካም ገጽታን የሚገነቡ ክልላዊና ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ልዩ ልዩ ሥራዎችን ያከናውናል፤

19/ Carries out various regional and national activities that enhance the institution's performance and build a positive image;

፳/ የኮሚሽኑን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

20/ Prepares the commission's plan and budget and submits it to the relevant authority; and implements when approved;

፳፩/ ውሎችን ይዋዋላል፤ የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

21/ Enters into contracts; own property; sue and be sued in his name;

፳፪/ የኮሚሽኑ አመራርና ባለሙያ ፣ የሰላምና ፀጥታ ፣ ሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባልየታጠቀውን የጦር መሣሪያ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ ያሰማራል፤

22/ Manages, controls, and deploys the weapons of the Commission's leadership and experts, peace and security, peacekeepers, and militia members;

፳፫/ ሌሎች ከኮሚሽኑ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሕጋዊ ተግባራት ያከናውናል።

23/ Performs other legal duties related to the purpose of the Commission.

፱. የኮሚሽኑ መዋቅራዊ አደረጃጀት

ኮሚሽኑ፦

፩/ የኮሚሽኑ ኮሚሽነርና ተጠሪነታቸው ለኮሚሽነሩ የሆኑ ምክትል ኮሚሽነሮች፤

፪/ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎችና የሥራ ክፍል ኃላፊዎች፤

፫/ የኮሚሽኑ አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ ሰላም አስከባሪ፣ ሚሊሻ አባላት፣ እና

፬/ ሲቪል ሠራተኞች፤ ይኖሩታል።

፲. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ መሠረት ለኮሚሽኑ የተሰጡ ተግባራትን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ የሚከተሉት ተጨማሪ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የኮሚሽን አመራሩን፣ ባለሙያውን፤ ሰላም አስከባሪውንና ሚሊሻ አባሉን ለሕገ-መንግሥቱና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ታማኝ፣ ታዛዥና ተገዥ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ይህንን እምነት የሚፈጥሩና የሚያሳድጉ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በቀጣይነት እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

ለ) መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ኮሚሽኑን ወክሎ ግንኙነት ያደርጋል፤

ሐ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

9. Structural Organization of the Commission

The Commission shall consist of:

1/ The Commissioner of the Commission and Deputy Commissioners who shall be accountable to the Commissioner;

2/ Various working units and heads of working units;

3/ The Commission's managemenet, experts, peacekeepers, militia members, and

4/ Civilian employees.

10. Powers and Duties of the Commissioner

1/ Coordinates, directs and implements the functions assigned to the Commission under Article 8 of this Proclamation;

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article 1 of this Article, the Commissioner shall have the following additional powers and duties:

A) Ensures that the leadership of the Commission, professionals, peacekeepers and militia members are loyal, obedient and submissive to the Constitution and the constitutional system, and ensures that capacity building activities that creates and enhances this trust are continuously carried out;

B) Liaises with governmental and non-governmental institutions on behalf of the Commission;

C) Prepares the Commission's annual work plan and budget and submits to the regional government; and implements when approved;

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደ በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል ፣በክልሉ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ሥራ ላይ ያውላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤

ሠ) የኮሚሽኑን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ዘገባ በሚመለከት ለቢሮው እና ለክልሉ ገንዘብ ቢሮ ያቀርባል፤

ረ) የዞን መምሪያ ኃላፊዎችን ምደባ ፣ ዝውውር እና ከኃላፊነት ማንሳት ለቢሮው አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል ፤

ሰ) በክልል ደረጃ ዋና መምሪያ ኃላፊዎችን፣ ዋና ክፍል ኃላፊዎችን፣ የዞን መምሪያ ዋና ክፍል ኃላፊዎችን እና የወረዳ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ሃላፊዎችን ምደባ መርምሮ ያጸድቃል፣ ያዛውራል፣ ያነሳል፤

ሸ) በየደረጃው የሚገኙ የሚሊሻ ባለሙያዎች፣ የቀጠና አስተባባሪዎች፣የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባላት ምልመላ፣ ቅጥር፣ ዕድገት፣ አስተዳደርና ስንብት ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸም ያደርጋል፤

ቀ) የሲቪል አስተዳደር ሠራተኞች ምልመላ፣ ቅጥር፣ ዲሲፕሊን፣ አስተዳደርና ስንብት በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

በ) በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራ የተሰናበቱ፣ ከኃላፊነት የተነሱ፣ የተዛወሩ መለዮ ለባሾች በሚያቀርቧቸዉ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ላይ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

ተ) ሌሎች ከሥልጣንና ኃላፊነቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

D) Spends money in accordance with the budget approved for the Commission, and shall implement, control, and manage in accordance with the Financial Management Law of the State Government;

E) Submits reports on the work and financial activities of the Commission to the Bureau and the Regional Finance Office;

F) Submits the assignment, transfer and dismissal of Zonal Department Heads to the Bureau for approval;

G) Examines, approves, transfers and dismisses the heads of the main departments, heads of the main sections, heads of the main sections of the zonal departments and heads of the woreda militia offices at the regional level;

H) Ensures that the recruitment, employment, promotion, administration and dismissal of militia experts, zone coordinators, peacekeepers and militia members at all levels are carried out in accordance with the regulation and directive issued pursuant to this proclamation;

I) Ensures that the recruitment, employment, discipline, administration and dismissal of civil administration employees are carried out in accordance with the regional civil service law;

J) Gives final decisions on complaints and petitions filed by soldiers who have been dismissed, removed from their duties or transferred due to disciplinary offenses in accordance with the relevant law;

K) Performs other duties related to his authority and responsibility.

፲፩. የምክትል ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባራት

፩/ ኮሚሽኑ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝ መጠን ከአንድ በላይ ምክትል ኮሚሽነሮች የሚኖሩት ሆኖ ወታደራዊ፣ ሎጅስቲክሳዊና አስተዳደራዊ የሥራ ክፍሎችን ያስተባብራሉ፣ ይመራሉ፤

፪/ የኮሚሽኑን ሥራዎች በማቀድ፣በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ያግዛሉ፤

፫/ ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ውክልና የተሰጠው ወይም በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ኮሚሽነሩ ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሠራል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የተደነገገው ቢኖርም ሹመቱ በተመሳሳይ ቀን የተሰጠ ከሆነ ከተሿሚዎች መካከል ሴት ካለች ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ በተገለፀው መሠረት መለየት ካልተቻለ የበለጠ የስራ ልምድ ያለው የሚመራ ይሆናል፡፡

ክፍል ሦስት

ስለኮሚሽኑ አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ ሰላም አስከባሪና ሚሊሻ አባላት አስተዳደር

፲፪. ስለ ምልመላና ምደባ

፩/ ኮሚሽኑ ለሰላም አስከባሪና ለሚሊሻነት ብቁና ፈቃደኛ የሆኑ፣ ቋሚ የቀበሌው ነዋሪ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ሰዎችን በሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ይመለምላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

11.Powers and Duties of Deputy Commissioners

1/ The Commission shall have more than one Deputy Commissioner as may be necessary for its work, and shall coordinate and direct the military, logistical and administrative departments;

2/ They shall assist the Commissioner in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the Commission;

3/ In the absence of the Commissioner, the Deputy Commissioner who has been delegated or has priority in appointment shall act in his place;

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article 3 of this Article, if the appointment is made on the same day, if there is a woman among the appointees, priority shall be given to the woman;

5/ If it is not possible to distinguish according to the provisions of Sub-Articles 3 and 4 of this Article, the person with more work experience shall be appointed.

PART THREE

About the Administration of The Commission's Leaders, Experts, Peacekeepers and Militia Members

12.Recruitment and Assignment

1/ The Commission shall recruit, through direct public participation, persons who are qualified and willing to serve as peacekeepers and militia, and who can provide evidence of being permanent residents of the kebele; the detail shall be determined in regulation;

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ለኮሚሽኑ አመራርነት ወይም ባለሙያነት ብቁ የሆኑ ሰዎችን መልምሎ ይመድባል፤ የቅጥር ውል ይፈጽማል፤ ያስተዳድራል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

፲፫. ስለሥልጠና

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት መሠረታዊ የሚሊሺያነት ሥልጠና ይሰጠዋል፤

፪/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪ፣ የሚሊሻ አባል ለተመለመለበት ኃላፊነት ብቁ የሚያደርገው የአመራር ሥልጠና ይሰጠዋል፡፡

፲፬. ስለ ቃለ መሃላ

ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል ለተልዕኮ የሚያበቃውን ሥልጠና እንዳጠናቀቀ ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ ማንኛውንም ህገ ወጥ ድርጊት በመከላከል በታማኝነት፣ በሕዝባዊ ወገንተኝነትና ጀግንነት ለማገልገል ዝግጁ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቃለ-መሃላ ይፈጽማል፡፡

፲፭. የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባላት መብቶች

፩/ ማንኛውም መለዮ ለባሽ የኮሚሽኑ አመራር እና ሙያተኛ ወታደራዊ ጥቅማጥቅሞችን ፣ልዩ ልዩ ክፍያዎችንና አገልግሎቶችን ያገኛል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article 1 of this Article, the Commission shall recruit and assign persons who are qualified to serve as leaders or professionals of the Commission; recruit employment contracts; and administer them. The detail shall be determined in regulation.

13. Training

1/ Every Commission leader, professional, peacekeeper and militia member shall be provided with basic militia training before starting their service;

2/ Every Commission leader, professional, peacekeeper and militia member shall be provided with leadership training that will make him qualified for the duties for which he has been recruited.

14. Oath

Any member of the Commission's leadership, professional, peacekeeper, and militia shall, upon completion of the training required for the mission, take an oath to serve with loyalty, patriotism, and bravery, defending the Constitution and the constitutional order from any illegal acts that threaten it.

15. Rights of the Commission's Leaders, Professionals, Peacekeepers and Militia Members

1/ Any member of the Commission's Soldier, leader and professional shall receive military benefits, various payments and services; the details shall be determined in regulation;

፪/ ማንኛውም በአገልግሎት ላይ የሚገኝ ደሞዝተኛ የኮሚሽኑ አመራርና ሙያተኛ የጤና እክል ሲያጋጥመው ለራሱ፣ ለትዳር አጋሩና ከ18 አመት በታች ለሆኑ ልጆቹ በመንግሥት ወጭ ነፃ የህክምና አገልግሎት ያገኛል፤

2/ Any salaried Commission leader and professional who is in service shall receive free medical care at government expense for himself, his spouse and his children under the age of 18 years;

፫/ ማንኛውም የስምሪት ግዳጅ ላይ የሚገኝ የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል በግዳጅ ላይ ተሳታፊ ሆኖ ጉዳት ሲደርስበት ወይም ህመም ቢያጋጥመዉ በመንግሥት የህክምና ተቋማት ነጻ የህክምና አገልግሎት ያገኛል፤

3/ Any Commission leader, professional, peacekeeper and militia member who is in service of mission and suffers an injury or illness while participating in the service shall receive free medical care at government medical facilities;

፬/ ማንኛውም የሚሊሻ አባል በግዳጅ ወቅት ስምሪት ላይ ለቆየባቸው ጊዚያት ማካካሻ የሚሆን ልዩ ልዩ ድጋፎችንና አገልግሎቶችን በሚኖርበት አካባቢ በመንግስት እና ማሕበረሰብ ተሳትፎ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

4/ Any militia member shall be provided with various supports and services in the area where he lives to compensate for the time he has been in service during the mission.

፭/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል የተሰጠውን ተልዕኮ ወይም ግዳጅ ከመወጣት ጋር በቀጥታ በተያያዘ የወንጀልና የፍትሐብሄር ተጠያቂነት ኮሚሽኑ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሕግ ድጋፍ እንዲያገኝ ይሠራል፤

5/ Any member of the Commission, professional, peacekeeper and militia member directly related to the performance of the assigned mission or duty shall be provided with legal assistance for Criminal and Civil Liability incurred in accordance with the relevant law;

፮/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያና የሰላም አስከባሪ ዓመታዊና ልዩ ልዩ ፈቃዶችን የማግኘት መብት አለው፤

6/ Any member of the Commission, professional and peacekeeper shall have the right to obtain annual and other leaves;

፯/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ንዑስ አንቀጽ ፮ የተዘረዘሩ መብቶች ዝርዝር ጉዳይ በደምብ ይወሰናል፤

7/ The details of the rights listed in Sub-Articles 1 to 6 of this Article shall be determined by regulation.

ፐ/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል በስምሪት ላይ እያለ በሚደርስበት የአካል ጉዳት ወይም የህይወት መሰዋትነት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ድጎማዎችንና ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብት አለው።

፲፮. ስለ ኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪና ሚሊሻ አባላት ግዴታ

ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል፦

፩/ በማናቸውም ጊዜ ለሕግና ሕገ-መንግሥቱ ተገዥ የመሆን፤

፪/ ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን የማክበር፣ የማስከበር እና ከአደጋ የመጠበቅ፤

፫/ የሃገሪቱን፣ የክልሉንና የኮሚሽኑን ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ሕጋዊ ትዕዛዞች የማክበርና የማስከበር፤

፬/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ቢያንስ ለሰባት ዓመታት የማገልገል፤

፭/ ኢ-ሰብዓዊ ወይም ክብርን ከሚነካ ማንኛውም ዓይነት ንግግር፣ አያያዝ ወይም ድርጊት ራሱን በማራቅ ተልዕኮዉን በሕግ አግባብ ብቻ የመወጣት፤

፮/ ተግባሩን ሲያከናውን ከማንኛውም ዓይነት ወገንተኝነት ነፃ የመሆን፤

፯/ የክልሉን ሰላም እና ደህንነት ከማረጋገጥ በተጨማሪ በሀገሪቱ በሚፈጠሩ አገራዊ ችግሮች ጥሪ ሲደረግለት ከፌደራል መከላከያ ሰራዊቱ እና ከሌሎች የፀጥታ አካላት ጋር የመሰለፍና ጥቃትን የመከላከል፤

8/ Any member of the Commission, professional, peacekeeper and militia member shall have the right to receive subsidies and benefits in accordance with the relevant law in the event of physical injury or loss of life sustained while on duty.

16. Obligations of the Commission Leadership, Experts, Peacekeepers and Militia members

Any Commission leadership; proffessional, peacekeeper and militia member of the Commission:

1/ To be subject to the law and the Constitution at all times;

2/ To respect, uphold and protect the Constitution and the constitutional order;

3/ To respect and enforce the laws, regulations, directives, and legal orders of the country, the region, and the Commission;

4/ To serve for at least seven years as a member of the Commission or proffessional;

5/ To refrain from any speech, treatment, or action that is inhuman or degrading, and to carry out his duties only in accordance with the law;

6/ To be free from any form of bias while performing his duties;

7/ To join the Federal Defense Forces and other security forces when called upon to do so in the event of national problems in the country;

፰/ የተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋ ሲያጋጥም ከሌሎች የጸጥታ ተቋማትና ከሚመለከታቸው የመንግሥት የአስተዳደር አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ የመስጠት ፤

፱/ ለተልዕኮ ማስፈጸሚያ የተሰጠውን የጦር መሳሪያን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት ንብረት እና ሌሎች ሎጅስቲክስ ነገሮችን ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ እንዲውል የማድረግ፤

፲/ በመንግሥት የተሰጠውን ማንኛውንም ዓይነት የጦር መሳሪያ ከመሸጥ፣ ከመለወጥ፣ ከማከራየት፣ በትውስት ከመስጠት እና ከማበላሸት መቆጠብና ሌሎች ይህን ፈጽመው ሲገኙ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፤

፲፩/ በሥራው ምክንያት የሚያውቃቸውን መንግሥታዊና ተቋማዊ ሚስጥሮች የመጠበቅ፤

፲፪/ በሕግ መሠረት የሚሰጡ ተግባራትን ተቀብሎ የመፈጸም፤ ግዴታ አለበት።።

፲፯. ስለ አገልግሎት ዘመንና የጡረታ መውጫ ዕድሜ

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ ደመወዝተኛ አመራር ወይም ባለሙያ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ ቢያንስ ለሰባት ዓመት የሚያገለግል ይሆናል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመራሩ ወይም ባለሙያው የሰባት ዓመት ግዴታውን ሳይጨርስ አቋርጦ ቢወጣ ተቋሙ ለረጅም ጊዜ ሥልጠና ያወጣው ወጪ ታስቦ እንዲመልስ ይደረጋል፤

፫/ በየትኛውም እርከን የሚገኝ የኮሚሽኑ ደመወዝተኛ አመራር፤ ባለሙያና የቀጠና አስተባባሪ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሃምሳ አምስት ዓመት ይሆናል፤

8/ To provide support in coordination with other security institutions and relevant government administrative bodies in the event of natural and man-made disasters;

9/ To ensure that any property and other logistics, including weapons, provided for the implementation of the mission, are used only for authorized purposes;

10/ To refrain from selling, exchanging, renting, donating and destroying any weapons provided by the government and to inform the relevant body when others are found to have done so;

11/ He shall be obliged to protect governmental and institutional secrets that he knows in the course of his work;

12/ He shall be obliged to accept and carry out the duties assigned to him in accordance with the law.

17. Regarding the period of service and retirement age

1/ Any salaried leader or professional of the Commission shall serve for a minimum of seven years from the date of his recruitment;

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article 1 of this Article, if the leader or professional resigns before completing his seven-year term, the institution shall be reimbursed for the expenses incurred in his long-term training;

3/ The retirement age of a salaried leader, professional and sub-wereda coordinator of the Commission at any level shall be fifty-five years;

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተመለከተው ቢኖርም ጽሕፈት ቤቱ ለሥራ አስፈላጊ ነው ወይም በቀላሉ ሊተካ አይችልም ብሎ ያመነበትን አመራር ወይም ክፍል ኃላፊ ወይም ባለሙያ ወይም ቀጠና አስተባባሪ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከሦስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ደመወዝተኛ የኮሚሽኑ አመራር፤ ባለሙያ እና የቀጠና አስተባባሪ ከሃያ አምስት አመት በላይ የአገልግሎት ዘመን ካለው የጡረታ መውጫ ዕድሜው አምስት አመትና በታች ሲቀረው በራሱ ፈቃድ ጡረታ ለመውጣት ሊያመለክት ይችላል፤

፮/ ማንኛውም የሰላም አስከባሪ አባል በሃምሳ ዓመት በክብር እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡ አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

፯/ ማንኛውም የሚሊሻ አባል በሀምሳ አምስት ዓመት በክብር እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡ አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

፲፰. ስለ ካሳ፣ ድጎማና ጡረታ

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ የውል ግዴታ የገባበትን የአገልግሎት ዘመን ጨርሶ ከሥራ ሲሰናበት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ይሰጠዋል፤

፪/ ማንኛውም የኮሚሽኑ መለዮ ለባሽ አመራር ወይም ባለሙያ በታወቀ የጸጥታ ስምሪት ላይ እያለ የተሰዋ እንደሆነ መብቱ በወታደራዊ የጡረታ ሕግ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article 3 of this Article, the Office may extend the retirement age for a period not exceeding three years for a senior executive or department head, professional or regional coordinator who it considers to be essential for the work or cannot be easily replaced;

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article 3 of this Article, any salaried executive, professional or regional coordinator of the Commission who has served for more than twenty-five years may apply for retirement of his own free will when he has five years or less remaining before his retirement age;

6/ Any member of the peacekeeping force shall be honorably discharged at the age of fifty years. The performance shall be determined in regulation.

7/ Any member of the militia shall be honorably discharged at the age of fifty-five years. The performance shall be determined in regulation.

18. Compensation, Allowances and Pensions

1/ Any member of the Commission's management or professional, upon termination of his term of service for which he has entered into a contractual obligation, shall be given appropriate answers to any questions raised by him in accordance with the relevant law;

2/ If any member of the Commission's management or professional is sacrificed while on a recognized security assignment, his entitlement shall be governed by the Military Pension Law;

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ወይም ሰላም አስከባሪ በስምሪት ላይ እያለ ሲሰዋ ሕጋዊ ወራሾቹ የስድስት ወር ደመወዝ በአንድ ጊዜ የሚከፈላቸውና ደሞዝተኛ የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ዘላቂ የጡረታ መብት የሚከበርለት ይሆናል፤

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article 2 of this article, if any member of the Commission management or professional or peacekeeper sacrifies while on duty, his legal heirs shall be paid six months' salary in one time and the salaried management of the Commission or professional shall be entitled to a permanent pension in accordance with the relevant law;

፬/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ወይም ሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል መንግሥት የሰጠውን ግዳጅ ተቀብሎ ሲፈፅም በደረሰበት ጥቃት ምክንያት ከስድስት ወር በላይ አድራሻው ከጠፋ ሕጋዊ ወራሾቹ ሙሉ በሙሉ የካሳና ድጎማ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤

4/ If any member of the Commission management or professional or peacekeeper or militia member, while performing his duties as assigned by the Government, loses his address for more than six months due to an attack, his legal heirs shall be entitled to full compensation and allowances;

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም አባል ከስድስት ወር በላይ የቆየው በደረሰበት ጥቃት ምክንያት ባልሆነ ወይም አስገዳጅ ባልሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ ለቤተሰቦቹ የተሰጠው ካሳና ድጎማ የሚመልሱ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

5/ In accordance with the provisions of Sub-Article 4 of this Article, if it is determined that any member has been absent for more than six months due to a reason other than the attack or for a reason that is not compelling, they shall be reimbursed for the compensation and allowances given to their families; the details shall be determined in regulation;

፮/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ወይም ሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል ተቋሙ በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ ሕጋዊ ወራሾቹን እንዲያስመዘግብ ይደረጋል፤ በማንኛውም ምክንያት ህይወቱ ቢያልፍ ሕጋዊ ወራሾቹ የሚመለከተው የሕግ አካል በሚወስነው ውሳኔ መሠረት ለወራሾች በሕግ የተፈቀዱ ክፍያዎች በቀጥታ እንዲከፈላቸው ይደረጋል፤

6/ Any Commission management or professional or peacekeeper or militia member shall be required to register his legal heirs on a form prepared by the institution; in the event of his death for any reason, the legal heirs shall be paid the legally authorized payments directly to the heirs in accordance with the decision of the relevant legal body;

ሷ/ ማንኛውም የኮሚሽኑ ደሞዝተኛ አመራር ወይም ባለሙያ በጸጥታ ስምሪት ላይ እያለ በደረሰበት ከፍተኛ የአካል ጉዳት ምክንያት ራሱን መርዳት የማይችል መሆኑ በታወቀ የመንግስት የህክምና ተቋም የህክምና ቦርድ ሲረጋገጥ የቦርድ መብቱ ተከብሮለት ይሰናበታል፤

ሸ/ ማንኛውም ሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል በጸጥታ ስምሪት ላይ እያለ በደረሰበት ከፍተኛ የአካል ጉዳት ምክንያት ራሱን መርዳት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ በመንግሥት በሚቋቋም ማዕከል በዘላቂነት እንዲጦር ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

፲፱. አገልግሎት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች አገልግሎቱ ሊቋረጥ ይችላል፡-

፩/ በራሱ ጊዜ ሲጠይቅ እና የቅጥር ውል ዘመኑ ሲያበቃ፤

፪/ በሞት ሲለይ፤

፫/ የስንብት ጥያቄ አቅርቦ ስንብቱ ሲጸድቅ፤

፬/ ከባድ ህመም ወይም ጉዳት ደርሶበት ለሚሊሻ ተቋሙ ተልዕኮ ብቁ አለመሆኑ በሐኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ፤

፭/ በዕድሜ ጣሪያ በጡረታ ሲገለል ወይም በክብር ሲሰናበት፤

፮/ በጠላት ተማርኮ ወይም ከጠላት ጋር በተደረገ ዉጊያ ጠፍቶ ለ6 ወራት ያህል ሁኔታዉ ያልታወቀ እንደሆነ ፤

፯/ ኮሚሽኑ የመዋቅር ለውጥ ወይም የአሠራር ማሻሻያ በማድረጉ ምክንያት በሥራው እንዲቀጥል ለማድረግ ሳይቻል ሲቀር፤

7/ Any Commission management or professional who is paid by the Commission and is unable to support himself due to a serious injury sustained while on security duty shall be discharged from the Board of Directors upon confirmation by a medical board of a recognized government medical institution;

8/ Any peacekeeper or militia member who is found to be incapable of supporting himself due to a serious physical injury sustained while on duty shall be permanently confined to a center established by the government. The details shall be determined in regulation.

19. Termination of Service

Any member of the Commission management, professional, peacekeeper and militia may have his service terminated for the following reasons:

1/ Upon his own request and upon the expiration of his employment contract;

2/ Upon death;

3/ When his request of resignation is approved;

4/ Upon a serious illness or injury and a medical board certifying that he is unfit for the mission of the militia institution;

5/ Upon retirement due to old age or honorable discharge;

6/ If he is surrendered by the enemy or missing in action with the enemy and his condition is unknown for 6 months;

7/ If the Commission is unable to continue his work due to structural changes or operational improvements;

ፐ/ በግዳጅ አፈጻጸም ወይም በዲስፕሊን ጉድለት ለአገልግሎት ብቁ አለመሆኑ በየደረጃው መሰናበቱ ሲረጋገጥ፤

ፑ/ ከግዳጅ አፈጻጸም ሁኔታ ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ በወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት ውሳኔ ጥፋተኛ ተብሎ ሲወሰን።

፳. ስለ ዲስፕሊን ጥፋትና ቅጣት

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተካተቱ ግዴታዎችንና ድንጋጌዎችን የተላለፈ እንደሆነ በኮሚሽኑ የዲሲፕሊን ደንብ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፤

፪/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ግዴታዎችን ሳይወጣ የቀረ እንደሆነ እንደ ጥፋቱ ክብደት በዲስፕሊን ተጠያቂ ይሆናል ዝርዝሩ በደንብ ወይም በመመሪያ ይወሰናል፤

፫/ የዲሲፕሊን ጥፋት ደረጃዎችን፣ አይነቶችን አጣርቶ ለውሳኔ የሚያቀርብ የዲስፕሊን አጣሪ ኮሚቴ በሁሉም ደረጃ እንዲቋቋም ይደረጋል፤ ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ይሆናል።

፳፩. አቤቱታ ስለማቅረብ

ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል የአስተዳደር በደል ደርሶብኛል የሚል ቅሬታ ካደረበት ውሳኔ ከሰጠው አካል አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሚገኘው ኃላፊ አቤቱታ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

8. If he is dismissed at any level due to compulsory service or disciplinary misconduct;

9. If he is convicted of a crime unrelated to compulsory service and is found guilty by a court decision.

20. Disciplinary Offenses and Punishments

1. Any member of the Commission's management, professional, peacekeeper, or militia who violates the obligations and provisions of the relevant laws shall be held accountable in accordance with the Commission's disciplinary regulations;
2. Any member of the Commission's management, professional, peacekeeper, or militia who fails to fulfill the obligations set forth in this proclamation shall be held disciplinary accountable in accordance with the severity of the offense. The details shall be determined by regulation or directive;
3. A disciplinary investigation committee shall be established at all levels to examine the levels and types of disciplinary offenses and submit them for decision; the details shall be determined by regulation.

21. Filing a Complaint

Any member of the Commission's management, professional, peacekeeper, or militia who has a complaint that he has been subjected to administrative misconduct has the right to file a complaint with the officer one level higher than the person who made the decision; the details will be determined by regulation.

ክፍል አራት
ስለ ኃላፊነት ዕድገት፣ የግዴታ አገልግሎት፣ ስንብት፣ ሜዳይና ምስክር ወረቀት

፳፪. ስለ ኃላፊነትና ዕድገት አሰጣጥ

፩/ የኃላፊነት ዕድገት ሲሰጥ ብቃትን፣ መልካም ሥነ-ምግባርንና አገልግሎትን መሠረት ባደረገ ውድድር ሆኖ ሚዛናዊ እና የሴቶችን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ መንገድ ይሆናል፤

፪/ የኮሚሽኑ ኮሚሽነርና የምክትል ኮሚሽነሮች በርዕሰ መስተዳደሩ ይሾማሉ፤

፫/ በክልል ደረጃ ዋና መምሪያ ኃላፊዎችና ዋና ክፍል ኃላፊዎች በኮሚሽነሩ ይመደባሉ፤

፬/ የዞን መምሪያ ኃላፊዎች በዞን ዋና አስተዳዳሪ ወይም በከተማ አስተዳደር ከንቲባ ታይቶ በኮሚሽኑ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተወስኖ ሲቀርብ በቢሮ ኃላፊው ይመደባሉ፤

፭/ የዞን መምሪያ ዋና ክፍል ኃላፊዎች በመምሪያ ማኔጅመንት ኮሚቴ ታይቶ በኮሚሽኑ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተወስኖ ይመደባሉ፤

፮/ የወረዳ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች በወረዳ አስተዳዳሪ ወይም በከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ታይቶ በዞን መምሪያ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተወስኖ በኮሚሽኑ ይመደባሉ፤

፯/ የወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት ክፍል ሃላፊዎች በወረዳው ማኔጅመንት ታይቶ በመምሪያ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተወስኖ ይመደባሉ።።

PART FOUR
Promotion, Compulsory Service, Discharge, Medals and Certificates

22. Regarding the Allocation of Responsibilities and Promotions

1. Promotions shall be based on competition based on merit, good conduct and service, in a fair manner and in a manner that ensures the participation of women.

2. The Commissioner and Deputy Commissioners of the Commission shall be appointed by the head of government;

3. At the regional level, the Heads of Departments and Heads of Divisions shall be appointed by the Commissioner;

4. The heads of the Zonal Departments shall be appointed by the Head of the Bureau upon the recommendation of the Zonal Chief Administrator or the Mayor of the City Administration and upon the recommendation of the Commission Management Committee;

5. The heads of the Zonal Departments shall be appointed upon the recommendation of Department Management Committee and approved by the Commission Management Committee;

6. The heads of the wereda militia offices are appointed by the wereda administrator or the mayor of the city administration, determined by the Zonal Department Management Committee, and assigned by the commission.

7. The heads of the Woreda Militia Office shall be appointed by the Woreda Management and determined by the Department Management Committee.

፰/ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የቀጠና መለዮ ለባሽ የባለሙያዎች ምደባ በምደባ የሚፈጸም ይሆናል፡ ፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፫. የግዴታ አገልግሎት

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ልዩ ስልጠና ወይም ትምህርት ተከታትሎ ከጨረሰ በኋላ በሥልጠና ወይም በትምህርት የቆየበትን ጊዜ ያህል የማገልገል ግዴታ አለበት፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪ እና ሚሊሻ አባል በክልሉ ወይም በሀገር ደረጃ በተፈጠረ የጸጥታ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የክተት ወይም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲታወጅ የማገልገል ግዴታ አለበት፤

፫/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል በክልሉ ወይም በፌዴራል መንግሥት ደረጃ በተፈጠረ የጸጥታ መታወክ ወይም በአገር መወረር ወይም በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የክተት ወይም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀበት ሁኔታ የሥራ መልቀቂያ ወይም ዝውውር ወይም የዓመት እረፍት ፈቃድ መጠየቅ አይችልም፡፡

፳፬. ከሥራ የማሰናበት ውሳኔ

አግባብ ባለው የዲስፕሊን አወሳሰን ሥነ-ሥርዓት ደረጃ አልፎ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ ፬፣ ፯፣ ፰ እና ፱ መሰረት አገልግሎት ሲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡-

8. The assignment of proffessionals to the regional, zonal, woreda and sub-wereda level shall be done through assignment. The details shall be determined by the directives.

23. Compulsory Service

1. Any member of the Commission's management or professional who has completed special training or education shall be obliged to serve for the period of time spent in training or education;

2. Notwithstanding the provisions of Article 17, Sub-Article 1 of this Proclamation, any member of the Commission management, professional, peacekeeper and militia shall be obliged to serve when a state of emergency is declared due to a security or natural disaster occurring at the regional or national level;

3. Any member of the Commission management, professional, peacekeeper and militia shall not be entitled to request resignation, transfer or annual leave in the event of a state of emergency occurring at the regional or federal level due to a security or natural disaster occurring at the regional or federal level.

24. Decision to dismiss

After the appropriate disciplinary procedure has been completed, the final decision on termination of service in accordance with Article 19, Sub-Articles 4, 7, 8 and 9 of this Proclamation shall be made in the following manner:

፩/ የመምሪያ ኃላፊ በዞን አስተዳዳሪ ወይም የከተማ አስተዳደር ከንቲባ አስተያየት ሰጭነት በኮሚሽኑ አቅራቢነት በቢሮ ኃላፊው ይወሰናል፤

፪/ በክልል የዋና መምሪያ ኃላፊዎችና ዋና ክፍል ኃላፊዎች፣ መለዮ ለባሽ ባለሙያዎች በኮሚሽኑ የሚወሰን ይሆናል፤

፫/ የዞን ሚሊሻ መምሪያ ዋና ክፍል ኃላፊዎች እና የወረዳ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በመምሪያው አቅራቢነት በኮሚሽኑ የሚወሰን ይሆናል፤

፬/ የወረዳ ክፍል ኃላፊዎች በመምሪያው ማኔጅመንት ኮሚቴ ይወሰናል፤

፭/ የቀጠና አስተባባሪና የሰላም አስከባሪ አባላት በወረዳው ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማኔጅመንት ኮሚቴ የሚወሰን ይሆናል፤

፮/ የሚሊሻ አባላትን በተመለከተ በአባላት አስተያየት ተሰጥቶ የመጨረሻ ውሳኔው በወረዳ ማኔጅመንት የሚሰጥ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

፳፭. ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ስለሚደረግ ዝውውር

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራርና ባለሙያ በጸጥታ ስራ ስምሪት ላይ ባለበት የአካል ጉዳት ደርሶበት በተቋሙ ላለመቀጠል አሳማኝ ምክንያቶች ሲያጋጥሙ ኮሚሽኑ ከሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኀብት ልማት ቢሮ ጋር በመነጋገር በሚመጥነው የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ መሠረት በየትኛውም የመንግስት ተቋም ውስጥ በቋሚነት ወይም በጊዚያዊነት ተዛውሮ እንዲመደብ ሊያደርገው ይችላል።

1/ The head of a department shall be determined by the head of the bureau upon the recommendation of the Zonal Administrator or the Mayor of a City Administration, upon the recommendation of the Commission;

2/ The heads of regional departments and heads of main sections, and the special proffessionals shall be determined by the Commission;

3/ The heads of the main section of the zonal militia department and the head of the woreda militia office shall be determined by the commission upon the recommendation of the department;

4/ The heads of the woreda sections shall be determined by the department management committee;

5/ The members of the sub-wereda coordinator and peacekeepers shall be determined by the management committee of the woreda militia office;

6/ The final decision regarding militia members will be made by the wereda management after receiving feedback from the members; the details will be determined by regulation.

25. Transfer to another Governmental Institution

1/ In the event that any member of the Commission's management or professional is injured while on security duty and has compelling reasons for not continuing in the institution, the Commission may, in consultation with the Civil Service and Human Resources Development Bureau, transfer him to any government institution on a permanent or temporary basis, based on his educational background and work experience.

፪/ ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተዛወረ የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ መብቱና ግዴታው የተዛወረበት መስሪያ ቤት በሚተዳደርበት ሕግ የሚገዛ ይሆናል፡፡

፳፮. የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይና የምስክር ወረቀት

ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ በተሰለፈበት አውደ ውጊያ የዘወትር የጸጥታ ግዳጅ አፈጻጸም ከሚጠይቀው በላይ የሚያኮራ ጀግንነት ለፈጸመ ኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ወይም ሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል ሥራው በሚመጥነው ልክ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሽልማት ወይም የላቀ የሥራ ውጤት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፳፯. ስለ አገልግሎት ዘመን የምስክር ወረቀትና ማበረታቻ

ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ በዲስፕሊንና በሥራ አፈጻጸም ጉድለት የሌለበት ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል እንደየ አገልግሎት ዘመኑ የሚከተለው የአገልግሎት ዘመን የምስክር ወረቀትና ማበረታቻ የገንዘብ ሽልማት ይሰጠዋል፡-

፩/ ከ30 ዓመትና በላይ ላገለገለ የአገልግሎት ዘመን አንደኛ ደረጃ የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት፤

፪/ ከ25 አመት በላይ እስከ 29 ዓመት ላገለገለ የአገልግሎት ዘመን ሁለተኛ ደረጃ የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት፤

2/ The rights and obligations of the Commission's management or professional who is transferred to another government office shall be governed by the law governing the office to which he is transferred.

26. Battle Hero Medal and Certificate

A Commission management or professional or peacekeeper or militia member who has performed a bravery that goes beyond the ordinary performance of security duties in the battle where he was deployed, and shall be awarded the Battle Hero Medal or a certificate of outstanding performance, as appropriate to his work; the details shall implement in regulation.

27. Certificate and Incentive for Service Period

The details are to be determined in regulation and any Commission management, professional, peacekeeper and militia member who has no deficiencies in discipline and performance of duty shall be awarded the following certificate and incentive cash award for service period according to his service period as follows:

1/ First-class certificate and cash award for service period of 30 years and above;

2/ Second-class certificate and cash award for service period of more than 25 years and up to 29 years;

፫/ ከ20 አመት በላይ እስከ 24 ዓመት ላገለገለ የአገልግሎት ዘመን ሶስተኛ ደረጃ የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት፤

፬/ ከ15 አመት በላይ እስከ 19 ዓመት ላገለገለ የአገልግሎት ዘመን አራተኛ ደረጃ የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፰. ስለ በጀት

የኮሚሽኑ ዓመታዊ በጀት በክልሉ መንግሥት ይመደባል።

፳፱. ስለ ግዥና ንብረት አስተዳደር

፩/ ኮሚሽኑ የትኛዉንም ዓይነት ግዥ በመንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግጋት መሠረት ይፈጽማል፤

፪/ ኮሚሽኑ የመንግሥትን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ሕግጋት የተከተለ መዛግብት ይይዛል።

፴. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የተጀመሩ የዲሲፕሊን ጉዳዮች፣ የፍርድ ቤት ክርክሮችና ሌሎች ሂደቶች ጉዳዩ ሲጀመር በነበሩት ሕግጋት መሠረት ተጣርተው እልባት ያገኛሉ።

፴፩. ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፩፺፱፱ እና ማሻሻያዉ አዋጅ ቁጥር ፹፩/፩፺፱፭ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፤

3/ Third-level certificate and cash award for service of more than 20 years and up to 24 years;

4/ Fourth-level certificate and cash award for service of more than 15 years and up to 19 years.

PART FIVE

Miscellaneous Provisions

28. Budget

The annual budget of the Commission shall be allocated by the regional government.

29. Regarding Procurement and Asset Management

1/ The Commission shall carry out any type of procurement in accordance with the Government Procurement and Asset Management Laws;

2/ The Commission shall maintain records in accordance with the Government Finance and Asset Management Laws.

30. Transitional Provisions

Disciplinary cases, court disputes and other proceedings initiated before the effective date of this Proclamation shall be examined and resolved in accordance with the laws in force at the time the case was initiated.

31. Repealed and Inapplicable laws

1/ The Militia Office Establishment Proclamation No. 13/1998 and its amendment Proclamation No. 81/1995 are hereby repealed;

2/ Any law or practice that is inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation;

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ላይ የተደነገገው ቢኖርም የሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፩ሺ፱፻፹፰ እና ማሻሻያዉ አዋጅ ቁጥር ፹፩/፩ሺ፱፻፺፭ መሠረት የወጡ ደንብ እና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ እና በሌላ ደንብና መመሪያ እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፤

፴፪. መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፩ሺ፱፻፹፰ እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር ፹፩/፩ሺ፱፻፺፭ ለክልሉ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ተሰጥተው የነበሩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ለተቋቋመዉ ለክልሉ ሚሊሻ ኮሚሽን ተላልፈዋል፡፡

፴፫. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስችል ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፴፬. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles 1 and 2 of this Article, the rules and regulations issued pursuant to the Militia Office Establishment Proclamation No. 13/1996 and its amendment Proclamation No. 81/1993 shall, unless they contradict with proclamation apply until they are replaced by other regulation and directive;

32. Transfer of rights and obligations

The rights and obligations granted to the Regional Militia Office by Proclamation No. 13/2006 and its amendment Proclamation No. 811/2003 on the establishment and determination of the powers and functions of the Amhara National Regional State Militia Office have been transferred to the Regional Militia Commission re-established in accordance with this Proclamation.

33. Power to issue Regulations

The Regional Government Council may issue regulations to implement this Proclamation.

34. Power to issue Directive

The Bureau may issue detailed directive to implement this Proclamation and any regulation issued pursuant to this Proclamation.

፴፭. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ሚያዚያ 20 ፪ሺ፲፰ ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር

ቀን መጋቢት ፲፮/፪ሺ፲፰ዓ.ም

አረጋ ከበደ ለጋስ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚደንት

35. Effective Date of Proclamation

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Regional Government Gazette as of 28th day of April, 2026.

Done at Bahir Dar,

March 25 /2026

Arega Kebede Legas

President of the Amhara National Regional State.